# ከባለቤቱ ያወቀ ፣ ቡዳ ነው በላቸው

እሰይ የኔ መንጋ ፣ እሰይ የኔ ውሻ
እስከመቼ ድረስ ፣ ትደበቅ ከዋሻ
አንተነትክን አውጅ ፣ ይወቀው አበሻ
እንኳን ጃስ ተብለህ ፣ ታውቃለህ ጥቅሻ
ሺ ጊዜ ቢያወግዙህ ፣ ቢቀቡህ ጥቀርሻ
ጥርሸን አግጥጠህ ፣ ዘንጥል በንክሻ ።

እንኳንም አቤት አልክ ፣ ስምህን ሲጠሩ
መች አጣኸው አንተስ ፣ አሽሙር ሲናገሩ
ስምክን ባደባባይ ፣ አውጥተው ሲዘሩ
አስመስለህ ተነስ ፣ ጦር የወረወሩ
አበጀህ መንጋዬ ፣ አበጀህ ደፋሩ
ተነቃብን ሲሉ ፣ አንገት ያቀርቅሩ ።

እስቲ አንዳድ ጊዜ እንኳን ፣ አኩራኝ የኔ መንጋ
ብቻ ማንነትክን ፣ ስምህን አትዘንጋ
ስለ ስምህ ብለህ ፣ ጠንክረህ ተዋጋ
ባትጠራም እንኳን ፣ ዝም ብለህ ተንጋጋ
ብቻ ለዛ ቢስ ሁን ፣ በጠባ በነጋ
አንድ ቀን ያፈራል ፣ የድካምህ ዋጋ ።

ዘቅዝቀው ሰቀሉ ፣ ቢልህም ሃዋሳ
እሪ ቢል አበሻ ፣ ቢያበዛም ወቀሳ
አንተ ብቻ አስተውል ፣ ስምህን አትርሳ
አስፈላጊም ሲሆን ፣ ገጀራህን አንሳ
እንደመንደር ጋንጩር ፣ ልክ እንደ ጎረምሳ
አጫጭሰውና ፣ አቧራው ይነሳ ።

እናውቃለን ማለት ፣ ሆኖ እንጂ አመላቸው
ምን ክርክር ያሻል ፣ በማያገባቸው
እነዚህ ነፍጠኞች ፣ ስለማይገባቸው
ስለ ማንነትህ ፣ በደንብ አስረዳቸው
መንጋ መሆንህን ፣ አስረግጥላቸው
ከባለቤቱ ያወቀ ፣ ቡዳ ነው በላቸው ።

ታዛቢው
September 20, 2019